የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር7 አይሳኢታ ሐምሌ 1ቀን091	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	2nd Year No. 7 AYSAITA-8th July,2001

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የንብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ማቋቋሚያ

አዋጅ---------- ገጽ1

አዋጅ ቁጥር 01/09□□3 ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የህብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአፋር ብሔራዊ ክልል ተመሳሳይ ፍላጐት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ህብረተሰብ በመፍጠር ገንዘብን፣ እውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ቁጠባንና እርስ በእርስ መደጋገፍን የሚፈጥሩ የንብረት ሥራ ማህበራትን ማቋቋምና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ፣

አባላት በማህበራቸው አማካይነት ምርትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶችንና የብድር አገልግሎት እንዲያገኙና በነፃ ገበያ ተወዳድረው ምርታቸውን ወይም አገልግሎታቸውን በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ የሚያስችላቸውን ሁኔታ በማመቻቸት ለክልሉ ልማት ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጣው የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 191 መሠረት ለተቋቋመውና ወደፊትም በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቋቋሙ ማህበራት ድጋፍ የሚሰጥ የህብረት ሥራ ማህበራትን የሚያስፋፋና የሚያስተባብር አንድ የመንግስት አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9/3/3 - 10 መሠረት የሚከተውን አውጀል።

ክፍልአንድ

ጠቅላላ

1. አጭርርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የንብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ------ /09□□3 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጉሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካለሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. ማህበር ማለት በአዋጅ ቁጥር 17/09□□1መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ ማንኛውም የንብረት ሥራ ማህበርነው። በተለየም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል።

ሀ/ የከብት አርቢዎችን የከብት አርቢ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበራት፣

ለ/ የመኖሪያ ቤት የንብረት ሥራ ማህበራት፣

ሐ/ የኢንዱስትሪና የእደ ጥበብ የህብረት ሥራ ማህበራት፣

መ/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የንብረት ሥራ ማህበር፣

ሠ/ የሸማቾች የንብረት ሥራ ማህበር፣

ረ/ የዓሳ አስጋሪዎች የህብረት ሥራ ማህበር፣

ሰ/ የማዕድን የህብረት ሥራ ማህበራትና ሌሎች።

2. ክልል ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልል ማለት ነው።

3. ቢሮ ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የህብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ነው።

3. ስለ ቢሮው መቋቋምና ተጠሪነት

1. የአፋር ብሔራዊ ክልል የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ /ከዚህ በኋላ ቢሮው እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው የመንግስት መ/ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ቢሮው ተጠሪነቱ ለአፋር ክልላዊ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

4. የቢሮው መዋቅራዊ አደረጃጀት

1. ቢሮው በክልሉ መንግስት የሚሾም የቢሮ ኃላፊና ለሥራ የሚያስፈልጉ የቴክኒክና ድጋፍ ሰጭ በባለሙያዎች የታገዘ መዋቅር ይኖረዋል።

2. የቢሮው ዋና መ/ቤት በክልሉ ርዕሰ ከተማ ሠመራ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በዞንና በወረዳ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትይኖረዋል።

4. የቢሮው ዓላማዎች

1. ለክልሉ ህዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙ በአባላቱ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ የተለያዩ ዓይነት የንብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

2. የህብረት ሥራ ማህበራት አባላት የምርት ማሳደጊያዎችን ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ጥሬ እቃዎችን የገበያና ብድር አገልግሎቶችንና የመሳሰሉትን በማግኘት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉበት ሁኔታዎች ማመቻቸት፣

3. የህብረት ሥራ ማህበራት የምርት ውጤቶች ከአባለት በመግዛትና ለገበያ በማቅረብ የአባሎቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣

4. ማህበራት በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነው የራሳቸውን ችግር ከመፍታት ባሻገር ለክልሉ ልማት ጉልተሳትፎ እንዲኖራቸው የማህበራቱን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ተከታታይ ስልጠናዎች ሌሎች ሁለንተናው ድጋፎች ማድረግ።

ክፍል ሶስት

7. የቢሮው ስልጣንና ተግባር

1. የህብረት ሥራ ማህበራትን በሚመለከት የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ የጥናትና የምርምር ተግባራትን ያከናውናል። በህብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚጠቅሙና በአባላት ተሳትፎ የሚሠሩ የልማት ኘሮጀክቶች ያዘጋጃል። የአፈፃፀም ስትራቴጂና ቅደም ተከተል ያወጣል፣ሲፀድቅም በተግባር ያውላል።

2. በአባላት ፍላጐት መሠረት ማህበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል።

3. ማህበራት አስፈላጊና ወቅታዊ የገበያ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ በነፃ ገበያ ተወዳዳሪ ሆነው ተጠቃሚ የሚሆኑ ለክልሉ የኢኮኖሚ እድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

4. አባላት በህብረት ሥራ ማህበራቸው በኩል የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን የምርት ውጤቶችን አገልግሎቶችን በጥናት ላይ የተመሠረተ ብድር እንዲያገኙና ምርትና አገልግሎትን በተሻለ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

5. በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

6. የህብረት ሥራ በገጠሩና በከተማ ለማስፋፋትና ለማዳበር የሚያስችሉ ተከበታታይ የትምህርትና ስልጠና ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ለህብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ ለማህበራት ቅጥር ሠራተኞችና ለህብረት ሥራ ባለሙያዎች ይሰጣል።

7. ዓለም አቀፍ የህብረት ሥራ መርሆዎችን መሠረት በማድረግና የክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በአዋጅ ቁጥር 17/09□□1 መሠረት የተደራጀ ማህበራትን ይመዘግባል። የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፣ ይሰርዛል።

8. የህብረት ሥራ ማህበራት በሚዋህዱበት በሚለያዩበት ወይም በሚፈርሱበት ጊዜ በፌዴራል መንግስት በወጣው አዋጅ ቁጥር 17091 መሠረት እንዲፈፀም አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

9. የህብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እንዲጠናከር የሙያ እገዛ በመስጠት ገንዘብና ንብረታቸውን እንዳይባክን ጥረት ያደርጋል። ወቅታዊ የሂሳብ ምርመራ በማድረግ ያግዛል።

10. በተለያዩ የህብረት ሥራ ማህበራት የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችን በማዘጋጀት በየማህበራቱ ያከፋፍላል።

11. የህብረት ሥራ ማህበራትን የሚመለከቱ ሕጐችና ደንቦችን መመሪያዎችን በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል።

12. ህብረተሰቡ ስለህብረት ስራ ጽንስ ሃሳብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ በመገናኛ ብዙሀንና በሌሎች ዘዴዎች የትምህርትና የቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳል።

13. የቢሮውን እቅድና በጀት ያዘጋጃል። ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

14. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ይከሰሳል።

15. ቢሮውን በሚመለከት ረቂቅ ሕጐችና ደንቦች ለአፋር ብሔራዊ ክልል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያፀድቃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

16. ሴቶችን በህብረት ሥራ ማህበር በማሳተፍ ያነቃቃል፣ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል።

17. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያፈጽማል።

7. የቢሮ ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

የቢሮ ኃላፊው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ለቢሮው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የቢሮውን ስራዎች ይመራል፣ያስተዳድራል፣ይቆጣጠራል፣

2. የቢሮውን ያጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ የሥራ ኘሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

3. በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ሰናብታል።

4. ለቢሮው በተፈቀደው በጀት ሥራና እቅድ መሠረት የገንዘብ ክፍያ ይፈጽማል።

5. በሕጉ መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቢሮው ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል።

6. እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ቢሮው ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል።

7. የቢሮውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

8. ስለስራው አፈፃፀም በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል።

9. ቢሮው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ቢሮውን ይወክላል።

10. በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎች ይፈፀማል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. ስለበጀትና የሂሳብ መዛግብት

1. የቢሮው የገንዘብ ምንጭ መንግስትና ሌሎች ይሆናል።

2. ቢሮው የተሟላና ህጋዊ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

3. የቢሮ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም እሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

9. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. በተመሳሳይ ከዚህ በፊት የተለያዩ የህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀትና ለመመዝገብ ለሌሎች ቢሮዎች ተሰጥቶ የነበረው ስልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 171 እና በዚህ አዋጅ መሠረት ለህብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ተላልፎአል።

10. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ሁሉ ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የመተባበር ግዴታ አለበት።

11. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

12. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው ይህን አዋጅ በሚገባ ስራ ላይ ለማዋል የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

13. አዋጁን የማሻሻል ስልጣን

ይህ አዋጅ ሊሻሻል የሚችለው በክልሉ ምክር ቤት ብቻ ነው።

14. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ታህሳስ ቀን ....09 3 ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት

መዕሰ መስተዳድር